# ከታጠቅ ለነጻነት ሰኔ 28 2000 (07/05/08)

## ከሕዝባቸዉ ጋር ለመቆም የመረጡት አገር ወዳድ ቆራጥ የአየር ሃይል አባላት ምን ይላሉ?




ቃል በገባነዉ መሰረት ባሁኑ ሰዓት ደህንነታቸዉ ሊጠበቅበት በሚችል አገር የስደተኝነት መብት ያገኙትና ቀደም ብሎ የኢሕአዴግ ወታደራዊ ፍርድ ቤት የሞት ብይን የፈረደባቸዉ አራት የአየር ሃይል አባላት፡-

1. ሻምበል ሳሙኤል ጌታቸዉ
2. መቶ አለቃ ሃይማኖት ገብረማርያም
3. መቶ አለቃ ይትባረክ ታከለ እና
4. መቶ አለቃ ፍቅረሥላሴ ፍለቀ

ጋር ቃል አቀባያችን ያደረገዉን ቃለ ምልልስ ከዚህ ቀጥለን እናቀርባለን።



**ሻምበል ሳሙኤል ጌታቸዉ** ለተደረገላቸዉ ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ እ.አ.አ በ1997 ለበረራ ባለኝ ከፍተኛ ፍላጎት ወደ ኢትዮጵያ አየር ሃይል የገባሁ ሲሆን በ SF-260 እና በ L-39 በሚባሉ አዉሮፕላኖች ላይ ሥልጠናዬን ወስጄ

በ2000 ዓም በአብራሪነት የበረራ ክንፍ እና የም/መቶ አለቃነት ማዕረግ በማግኘት ተመርቄያለሁ።በመቀጠልም በሚግ 23 አዉሮፕላን ላይ ተጨማሪ ሥልጠና ወስጄ አየር ሃይሉን እስከ 2002ዓም አገልግያለሁኝ። ከዚያም ወደ ራሺያ በመሄድ በከፍተኛ ጄት አብራሪነት የSU-27 አዉሮፕላን አብራሪነት ሥልጠና ወስጄያለሁኝ።ከዚያ በኋላም አየር ሃይሉን በተዋጊ አብራሪነት በኢንተርሴፕተርነት እስከ 2007 ዓም ድረስ አገልግያለሁ። እንደሚታወቀዉ ወያኔ ይህን ያህል ደረጃ ድረስ አስተምሮ በከፍተኛ እንክብካቤና እንደ አይን ከሚጠብቃቸዉ እሴቶቹ አንዱ ለመሆን በቅቼ ነበር። ወያኔ ኢሕአዴግ ለሚያራምደዉ የዘር ፖለቲካ እና የአምባገነንነት አገዛዝ በተለይም በ2005 ዓም ምርጫ ማጭበርበር በኋላ ፍላጎቱን በሃይል ለማሳካት ተፍጨርጭሯል፣ የብዙ ንጹሃንን ሕይወት በቀን በአደባባይ ቀጥፏል፣ የአገሪቱን ሃብት ለባለ ሥልጣኖቹ መንደላቀቂያ አዉሏል፣ ብሎም አላስፈላጊ የሆነ የጎረቤት ሃገር ዉስጥ ጣልቃ በመግባት ህዝቡን ብሎም አገሪቱን ወደማትወጣበት አስቸጋሪ ጠባሳ እና የኑሮ ዉስብስብነት ዉስጥ ከትቷል።

አንድ ንፁህ ሕሊና ላለዉና ለሚያስተዉል ሰዉ የወያኔ ተግባርና መጨረሻዉ አላማ በግልጽ የሚታይ በመሆኑ ከዚህ አረመኔ እና ፋሽስታዊ ስርዓት ጋር ተንደላቆ ከመኖር ይልቅ ለህሊና ነፃነትና የታሪክ ተወቃሽ ላለመሆን ስል ከምወደዉና ከመከብረዉ የበረራ ሕይወት ተነጥዬ ቢያንስ የወያኔ ኢሕአዴግ ተባባሪ አለመሆኔን ለመግለጽ እራሴን ከሥርዐቱ አግልያለሁ ብለዋል።



**መ/አ ሓይማኖት ገብረማርያም** ለተደረገላቸዉ ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የተወለድኩት ኮረም (ትግራይ) ሲሆን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን በሻሸመኔ ከተማ ተከታትዬ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርቴን ደግሞ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ አጠናቅቄያለሁ ብለዋል።በነበራቸዉ የበረራ ፍቅርም አየር ሃይልን

እንደተቀላቀሉ ገልጸዋል። በአገር ዉስጥና በዉጭ አገር የበረራ ኮርሶች በመዉሰድ ሙያቸዉን እነዳሳደጉ ገልጸዉ ሆኖም በአንድ ወቅት ለኮርስ ቤሎሩስ ሄደዉ ሳለ ባልደረቦቻቸዉ ወደ አገር ቤት አልመለስም ብለዉ ሲወስኑ እሳቸዉ ግን ዝግጁ ስላልነበሩ መመለሳቸዉን አስረድተዋል። መንግሥትም በመመለሳቸዉ ያልጠበቁትን የገንዘብ ሽልማት እንደሰጣቸዉ ገልጸዋል። ይህ ግን የትግራይ ተወላጅ ከመሆናቸዉ ጋር ተደምሮ በተመልካች ዘንድ የኢሕአዴግ አጥባቂ ደጋፊ ናቸዉ የሚል ስም አሰጠኝ ብለዋል። እዉነቱን ግን የቅርብ የሥራ ባልደረቦቻቸዉና ጓደኞቻቸዉ እንደሚያዉቁ ገልጸዉ የኢሕአዴግ አምባገነናዊና በሙስና የተበከለ መንግሥት በሕዝባችንና እንዲሁም በጦሩ መሐል የሚፈጽመዉ በደል ያንገፈግፋቸዉ እንደነበር አምርረዉ ተናግረዋል። በአየር ሃይል ዉሰጥ ብቃት የሌላቸዉ ሰዎች ለሥርዐቱ ባላቸዉ ታማኝነትና በወገንተኝነት የሃላፊነት ቦታ ይዘዉ የሚያደርሱት በደል፣ እንዲሁም የካድሬዎች ከፋፋይ ፕሮፓጋንዳና ስለላ የሚያሳዝን ነዉ፣ ነገር ግን በይፋ መቃወም በተለይም ከትግራይ ለመነጨን ሰዎች እጅጉን ከባድ ነበር፣ ነገር ግን በመጨረሻ በዚህ ጨቋኝና አድሎአዊ መንግሥት አለመሳተፍ ምርጫዬ በመሆኑ አገሬን ጥዬ ለመሄድ ወሰንኩ ብለዋል።ስለወደፊቱም የትግለ ሁኔታ ሃሳባቸዉን ሲገልጹ ቢያንስ ሥርዓቱን የሚጠይቁ ያለበለዚያም የሚቃወሙ ብዙ የትግራይ ተወላጆች አሉ፣ ነገር ግን ጭቆናዉና ጭካኔዉ በኛ ላይ ይብሳልና በትችት ላይ ከማትኮር ይልቅ የትግራይ ሕዝብ በሚያደርገዉ ትግል ሌላዉ ኢትዮጵያዊ ሁኔታዉን እየተረዳ ሊደግፈዉና ሊያበረታታዉ ይገባል፣ ወደትግሉ የሚቀላቀሉት ላይ በማትኮር ሌሎቹን እንጋብዛለን ብዬ አምናለሁ ብለዋል።



**መ/አ ይትባረክ ታከለ** ለተደረገላቸዉ ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የተወለድኩት በአዲሰ አበባ በ1969 ዓም ሲሆን በቦሌ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን አጠናቅቄ በመቀጠልም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለአንድ ዓመት ስማር ቆይቼ ለበረራ ካለኝ ፍላጎትና ሃገሬን ለማገልገል ካለኝ ምኞት የተነሳ በ1990 ዓም አየር ሃይል ለበረራ ሙያ ተቀጠርኩ ብለዋል። የመጀመሪያ የበረራ ሥልጠና በኢትዮጵያ አየር መንገድ ወስደዉ የቀረዉን የበረራ ሥልጠና በአየር ሃይል በመጨረስ በተለያዩ የትራንስፖርት አይሮፕላኖች እና በመጨረሻም አንቶኖቭ 12 (AN-12) በሚባል የጦር አይሮፕላንና ትራንስፖርት ማመላለሻ አዉሮፕላን ላይ የበረራ ቆይታዎች እንዳደረጉ ገልጸዋል። በዚህም ጊዜ ዉስጥ ያከናወኗቸዉ ዋና ዋና ተግባራትን ሲያስረዱ በአገር ዉስጥ እና እንዲሁም በሶማሊያ  በነበረዉ የአሸባሪዎች ጦርነት ላይ በመሰማራት በተለያዩ የሶማሊያ ቦታዎች ለሰራዊቱ የትራንስፖርትና የተለያዩ አገልግሎቶች በመስጠት መቆየታቸዉን ገልጸዋል።

ሥርዐቱን ትቼ ለመሰደድ ያበቃኝ ምክንያቶች፦ አንደኛዉና ዋነኛዉ በሃገራችን በነበረዉ የግንቦት ወር 1997 ዓም የምርጫ ሂደት ዉስጥ አምባገነኑ የኢሕአዴግ መንግሥት ያደረገዉ የምርጫ ዘረፋ፤ እንዲሁም በወቅቱ ንፁሐን ሰላማዊ ሕዝቦች ላይ የተደረገዉ ጭፍጨፋ ሲሆን ሌላዉ ይህ አምባገነን መንግሥት የመከላከያ ሠራዊቱን ለራሱ ለኢሕአዴግ አገልጋይ ሆኖ እንዲቆይና በዘር በመፋፈል አብዛኛዉን ቁልፍ የሚባሉ የመከላከያ ቦታዎች በአንድ የብሔር የበላይነት እንዲመራ በማድረግና የራሱ የሥልጣን ዘመንን ለማስረዘም የሚያደርገዉ አምባገነናዊ ሂደት ሲሆኑ፤ ይህንኑ በመቃወም ከምወዳት ዉድ ሃገሬ ለመሰደድ በቅቻለሁ ብለዋል።

ይህን አምባገነናዊ ሥርዐት ለመቀየር ለወደፊቱ ያለን እቅድ በተለያዩ ሚዲያዎች አማካኝነት የመንግሥትን አምባገነናዊ ይዞታዎችና ድርጊቶቹን በየጊዜዉ በማጋለጥ ለመከላከያ ሠራዊቱ በትክክል ማስረዳት ነዉ ብለዋል። ለአየር ሃይል ባልልደረቦቼ የማስተላልፈዉ መልዕክትም ይህንን አምባገነናዊ መንግሥት ሁላችንም ልንቃወመዉ የሚገባ መሆኑንና ከሌሎች ጋር በአንድነት ይገባል በማለት የትግል ጥሪያቸዉን አቅርበዋል።



**መ/አ ፍቅረሥላሤ ፈለቀ** ለተደረገላቸዉ ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የተወለድኩት በጎንደር ከተማ በ1968 ዓም ሲሆን እድገቴም በደብረ ዘየት ከተማ ነዉ። ትምህርቴን በደብረዘይት ከተማ ካጠናቀኩ በሁዋላ የኢትዮጵያ አየር ሃይል ባወጣዉ የአዉሮፕላን በረራ ሥልጠና ማስታወቂያ መሠረት በነበረኛ የበረራ ፍላጎት ተወዳድሬ በሐምሌ 1990 ዓም ለበረራ ሥልጠና ገባሁ። ለሥልጠናዬ ወደ ኢትዮጵያ አየር መንገድ ተልኬ በ1992 ዓም የንግድ አዉሮፕላን አብራሪነት ላይሰንስ፣ የበረራ ክንፍና ዲፕሎማ አግኝቼ ተመረቅሁ። ከዛም ወደ አየር ሃይል በመመለስ የጀት አዉሮፕላን ስልጠና ከወሰድኩ በኋላ

ወደ ትራንስፖርት አዉሮፕላን እስኳድሮን በረዳት አብራሪነት ዳሽ - 5 አዉሮፕላን ላይ ተመደብኩ፤ ከዛም በአንቶኖቭ 12 እና 32 አዉሮፕላኖች ላይ ተመድቤ በረዳት አብራሪነት ከአየር ሃይል እስክወጣ ድረስ አገለግል ነበር።

አየር ሃይልን ትቼ ለመሰደድ ካበቃኝ ነገር የመከላከያ ሠራዊቱ ዋናዉ ዓላማ የአገሩን ሉዓላዊነት ድንበሩን ከመጠበቅ፤ የሕዝቡን ሰላም ከመጠበቅ ይልቅ ገዢዉን ፓርቲ ሥልጣን ላይ ለማቆየት የተቋቋመ ድርጅት ሆኖ አገኘሁት።ይህንንም በተለይ ከምርጫ 97 በኋላ፤ በግላጭ ለሠራዊቱ ይህ መንግሥት ከሌለ ሁላችንም የለንም፤ኢትዮጵያም የምትባል ሃገር አትኖርም በማለት ትዕዛዝና ተማጽኖዉን በየጊዜዉ በሚደረጉ ስብሰባዎች (ማደንዘዣዎች) ማሰማቱ ዋናዉ የሰራዊቱ ተግባር ወያኔን ሥልጣን ላይ ማቆየት መሆኑን ይናገራል።

አየር ሃይል የሞያተኛ ተቋም ሆኖ ሳለ ለበራሪዉም ለቴክኒሻኖችም ዋናዉ የወያኔ (ኢሕአዴግ) ወገንተኛ መሆን እንጂ ሙያዉ በሁለተኛ ደረጃ እንደሚታይ ይነገረን ነበር። ከዚሁም ሌላ በሃገሪቱ ሀብት በብዙ ገንዘብ የተገዙ አዉሮፕላኖች በአነስተኛ የመለዋወጫ ዕቃዎች ጉድለት ምክንያት ከጥቅም ዉጭ ይሆናሉ። በሌላ በኩል ግን ለባለሥልጣናት ምቾትና ለሚንፈላሰሱበት መኪና የበለጠ ወጪ ይወጣል።

ሌላዉ በትምህርት ደረጃም በአመራር ብቃት በሌላቸዉ የወያኔ ባለሥልጣናት የአመራር ድክመት ምክንያት የአየር ሃይል የሙያ ብቃት እየወረደ ተተኪ ማፍራት የማይቻልበት ደረጃ ተደርሷል።

ለማጠቃለል በወያኔ የበላይነት የሚመራዉ ይህ ተቋም በዘረኝነት የተከፋፈለ፣ የአንድ ጎሳ አባላት የበላይነት የሚመራ፣ ለሃገሪቱም ለሕዝቦቿ ምንም ግድ የሌለዉ፣ ሃገራችንን ወደ ጥፋት ጎዳና እየመራ ያለ በመሆኑ በተለይ ከምርጫ 97 በኋላ በሚያደርሰዉ የንፁሃን ግድያና አፈና በመባባሱ የዚህ ስርዓት ጥፋት ተባባሪ ላለመሆን፣ ከምወዳት ሃገሬ ለመሰደድ በቅቻለሁ።

ይህን ለመቀየር ወደፊት ለማድረግ የማስበዉ ኢትዮጵያን እያጠፋ ያለዉን መንግሥት ለመቀየር በሚደረገዉ የኢትዮጵያዉያን ትግል ዉስጥ አቅሜ በፈቀደዉ ሁሉ ለመተባበር ነዉ።

አየር ሃይል ለሚገኙ አባላት የማስተላልፈዉ መልዕክት በተለይ በዚህ ጊዜ የወያኔ መንግሥት የሃገራችንን መሬት እየቸረቸረ ጥፋቱ እየበዛ በመሆኑ እንዲቃወሙትና ለሃገራቸዉና ለህዝቦቿ ጥቅም እንዲቆሙ ነዉ ብለዋል።

